# የአዳም ረታ መንገድና ቁራ በ'ይወስዳል መንገድ ያመጣል መንገድ'

## ©ማርቆስ ዘመንበረልዑል

አዳም በዘመኑ ከተደነቁ፥ ዘግይተው መመስገን ጀምረው አሁን ላይ ከፍተኛ ቦታ ከተሰጣቸው ደራስያን መሐል ነው። "ይወስዳል መንገድ ያመጣል መንገድ" የተሰኘው መጽሐፍ ከደራሲው ሥራዎች አንዱ የሆነ የአጫጭር ታሪኮች መድብል ነው።

በብዙ መጻሕፍቱ ውስጥ ያሉ ገጸባሕርያቱ መበደል አከርካሪው የሆነ የጀርባ ታሪክ አላቸው። በበደል እና በሕይወት ፍትሕ አልባነት፥ ተስፋ በመቁረጥና በከንቱነት ስሜት ውስጥ ያለ አብሰርድ (Absurd) እይታ የሚንጸባረቅባቸው ናቸው። ይሄም በአዳም አጻጻፎች ላይ Existential ፍልስፍና ጎልቶ እንዲወጣ ያደርገዋል።

ይወስዳል መንገድ… ላይ ያሉ ገጸባሕርያት በመጥፎ እድል የተሳሰሩ ናቸው። አሣሪ ገጸባሕርይ ሆኖ ጎልቶ የሚወጣው ቁራ አብሣሬ ክፉ ሆኖ በሁሉም ታሪክ ውስጥ ሲገለጥ ይታያል። የቁራውን ተግባር በተወሰኑ ነጥቦች እንመልከት፦

➡ ቁራ ከላይ እንደተገለጠውና በብዙ ማኅበረሰባዊ ክቦች ውስጥም የሞትና የክፉ ነገሮች መገለጫ ነው። በመጽሐፉ ውስጥም በዚሁ ማኅበራዊ የማመን እሳቤ ይሄ ባለትልቅ መንቆር እና ግዙፍ ክንፍ ቁራ ለተለያዩ ገጸባሕርያት ሲታይ በመጽሐፉ አናነባለን። በክቡ ውስጥ ያለውን ማኅበረሰባዊ ኢማን (Superstitious thinking) ጎላ አድርጎ ለማሳየት ደራሲው ተጠቅሞበታል።

➡"የቁራ መላክተኛ" - አደራው ከተበላ፥ ከተረሳ መልዕክት ጋር በተያያዘም ቁራ ይጠቀሳል። ይሄንን በተቃረነ መልኩ በዚሁ መጽሐፍ ላይ ያለው ቁራ ሊደርሳቸው የሚገባውን መልዕክት (ክፉ እጣ ቢሆንም እንኳ) ለገጸባሕርያቱ ሲያመለክት ይንጸባረቃል።

➡ አዳም በሕጽናዊ አጻጻፍ የትሥሥር መድረክ ዘርግቷል። የተዘረጋው ትሥሥር በደንብ የጎለበተው በሎሚ ሽታ እና በዚሁ ይወስዳል መንገድ ልብ ወለዶች ላይ ይመስለኛል።

(የመጀመሪያውን በሌላ ጊዜ እንመለስበታለን።) በዚህ ልብወለድ ላይ በፍጹም የማይገናኙ የሚመስሉ አጭር ታሪኮች (በውስጣቸው ሌሎች ግልገል ታሪክች ያሏቸውን ያስተሳስራል።
ብዙ አንባብያን "በየቦታው ያለአግባብ የገባው ቁራ" ትርጉም የማይሰጥ መሆኑን ሲናገሩ አደምጣለሁ። ነገር ግን ቁራው 'ብዙም ቦታ ያልተሰጠው 'የታሪኮቹ ትሥሥር ፈጣሪ በመሆን ሕጽናዊ አጻጻፍን ወደሌላ ደረጃ ከፍ ያደርገዋል።

ቀደም ብለን እንዳነሳነው እነዚህን ጥቃቅን ጭብጦች ያሏቸው የተለያዩ አጫጭር ታሪኮች ውስጥ ያሉ ገጸባሕርያት የሚያጣምሯቸው ክፉ እጣ እና ይሄው እንደነገሩ የገባ የሚመስል እንስሳ ናቸው። ይሄም በደምሳሳው የመጽሐፉን ገዘፍ ያለ ጭብጥና ዋና ገጸባሕርይ ትሥሥሩን ራሱን ያደርገዋል።